# "አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች ስትፈትሻቸው ከሰፈር ዕድር
# የተሻለ ጥንካሬ የላቸውም"

ዶ/ር ንጋት አስፋው ፖለቲከኛና ምሁር

በይርጋ አበበ

ዶክተር ንጋት አስፋው ትውልድ እና እድገታቸው አዲስ አበባ ሲሆን አንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያለውን ትምህርታቸውን የተማሩትም እዚሁ አዲስ አበባ በሚገኙ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ሲሆን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የተከታተሉት ደግሞ በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ ነው። ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በምስራቅ እና ምዕራብ አውሮፓ ተከታትለዋል። በተመረቁበት የማናጅመንት ትምህርትም በአውሮፓ የተለያዩ አገራት በስራ ላይ ከቆዩ በኋላ ከ20 ዓመት በፊት ወደ አገራቸው ተመልሰው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ሲያስተምሩ ቆይተዋል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከሚገኙ የተለያዩ የግል ዩኒቨርስቲዎች የማስትሬት ዲግሪ ተማሪዎችን በማስተማርና በአማካሪነት (Advisor ሆነው) እያገለገሉ ይገኛሉ።

በፖለቲካ ህይወታቸውም ቀደም ሲል አንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አባል እና አመራር ሆነው ሰርተዋል። በቀደመው ስርዓት ደግሞ የደርግን መንግስት በመቃወማቸው ለእስር እና ለግርፋት ተዳርገው እንደነበር ይናገራሉ። አንጋፋው ምሁር እና ፖለቲከኛ ዶክተር ንጋት አስፋው በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ፣ በቅርቡ ስለተከበረው የአድዋ ድል ውጤት እና በኢትዮጵያ ስላለው የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ በመኖሪያ ቤታቸው ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥዋል። የቃለ ምልልሱን ሙሉ ክፍል ከዚህ በታች አቅርበነዋል።

ሰንደቅ፡- የፖለቲካ ተሳትፎ ያለዎት ምሁር ነዎትና ወደ ዋናው ውይይታችን ከመግባታችን በፊት ፖለቲካን መቼ ነው የጀመሩት?

ዶክተር ንጋት፡- በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጀምሮ ነው መሳተፍ የጀመርኩት። ያደኩበት ነው ማለት እችላለሁ። ብዙ ዘመን ባልታሰርም ደርግ በአሰቃቂ ሁኔታ ገርፎኛል። ያ ያረካሁበት የአገሬ ፖለቲካ ብዙ ነገሮችን አሳልፏል። አሁንም በተቃዋሚ ጎራ አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ ፓርቲ ከመፍረሱ በፊት አመራር ነበርኩ። አንድነት እንደማንኛውም ታዳጊ አገር ተቃዋሚ ፓርቲዎች እሱም የመፍረስ እጣ ገጥሞት ፈርሷል። በሶስተኛው ዓለም አገራት የፖለቲካ ፓርቲዎች ህልውና አሳሳቢ ነው። መውደቅ፣ መፍረስ እና መነሳት አለ። አንድነትም በውጫዊና ውስጣዊ ችግሮች ፈርሷል። ለምን ፈረሰ እንዴት ፈረሰ የሚለው ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ አልገባም። ስለዚህ አንድነት ስለፈረሰ እኔም መፍረስ የለብኝምና አሁን ሁኔታውን እያጠናሁና የፓርቲዎቹን ፕሮግራም፣ ደንብ እና የአገሬን ሁኔታስ ለመፍታት እንቅስቃው ምን ይመስላል? የሚሉትን መርምሬ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአንዱ የተቃዋሚ ጎራ ውስጥ እሳተፋለሁ የሚል ዝግጅት ላይ ነው ያለሁት። ለረጅም ዓመታት ሳራምደው የነበረው አቋሜ ሰላማዊ እና ሰላማዊ ትግል ብቻ የሚል ሲሆን አባል እሆንበታለሁ ብዬ የማስበው ፓርቲም በፕሮግራሙ ሰላማዊ ትግልን ብቻ የሚያራምድ ሊሆን ይገባዋል። እልህ፣ ቂም በቀል እና ነፍጥ ያነገበን ፖለቲካ እልደግፈውምም በዚህ መንገድ የሚመጡትንም በግሌ እዋጋቸዋለሁ።

ሰንደቅ፡- እርስዎ ፈርሷል የሚሉትን አንድነት ለፍትህ እና ለዴሞክራሲ ፓርቲን ጨምሮ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመውደቅና በመንገዳገድ ላይ ያሳለፉ ናቸው ይባላል። በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከ 60 በላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሉ። የተቃዋሚ ፓርቲዎቹ በቁጥር መብዛት ለአገሪቱ ፖለቲካ አስተዋጽኦው ምንድን ነው?

ዶክተር ንጋት፡- እንግዲህ በአገራችን ውስጥ እንዳልከው ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሉ። ምንም በለው ምን ግን በፕሮግራም ደረጃ ደግሞ እጅግ የተቀራረበ ሆኖ ነው የምታገኘው። የአገሪቱ ዋናው ስንቅ እዛ ባለው የእነሱ ፕሮግራም ላይ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምን ስንቅ አቀረቡለት? በምን በምን መልኩ ህዝቡን ሊያታግሉ ይችላሉ? የኢኮኖሚ ፕሮግራማቸው ምን ይመስላል? የፖለቲካ ፍልስፍናቸውስ ምን ይመስላል? በሌሎች ማህራዊ መስኮችስ ያላቸው ፕሮግራም ምን ይመስላል? እውን የዚህችን አገር ህዝብ እና ታሪክ እንዲሁም ችግሯን መሰረት ያደረገ ነው ወይስ ከውጭ የተኮረጀ ፕሮግራም ነው የቀረጹት? ሁሉንም ችግሮች ሊፈታ የሚችል የፖለቲካ ፕሮግራም ነው የሚያስፈልገው። ይህን በተመለከተ ነው እኔም ጥናት እያደረኩ ያለሁት። መብዛታቸውን በተመለከተ ከመብት አንጻር ይብዛ እንዲያውም ያንሳል። ነገር ግን ከጥንካሬ አኳያ፣ ስርዓቱን ማለትም ገዥውን መደብ ከማየት አኳያ፣ የህዝቡን መሰረታዊ ጥያቄና ፍላጎት ከማየት አኳያ ብዙ ነገር ይቀራል። ስለዚህ ተወደደም ተጠላ እነዚህ በፖሮግራም የሚመሳሰሉ ድርጅቶች ወደ አንድ አካባቢ መምጣት አለባቸው። አሁን እየተደረገ ያለውም ይህንን ለማምጣት ነው። ሁሉም ሊብራል ዴሞክራሲ እንከተላለን ይላል፤ በመካላቸው ልዩነት ሳይኖር ትንንሽ ዘውድን በኪስ ይዞ መዞር ማለት ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ እነዚህን የፖለቲካ ድርጅቶች ስፈተሹ በአብዛኛው እርባና የላቸውም። ድርጅታዊ መዋቅራቸውን ከሴል አንስተህ እስከ ከፍተኛ የፖሊት ቢሯቸው ቢታዩ ከአንድ የሰፈር እድር የተሻለ ጥንካሬ የላቸውም። እኔ በእርግጠኝነት ነው የምናገረው። እኔ በዚያ በኩል ነው የመጣሁት። አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ እጅግ ግዙፍ ፓርቲ ነበር። እጅግ ከፍተኛ ምሁራንን ያሰባሰበ እና ከሴል አንስቶ አገር አቀፍ ድርጅታዊ መዋቅር ያቀፈ ፓርቲ ነበር። ይህን ስርዓት ለመጣል በሚገባ የተደራጀ ፓርቲ ነበር። ስለዚህ ስርዓቱ (ኢህአዴግን) ለዴሞክራሲ እና ለመድብለ ፓርቲ ስርዓት የቆመ ስርዓት ባለመሆኑ እዛ ውስጥ (አንድነት ፓርቲን ለማለት ነው) ቅጥረኞች ገብተው ሊያንኮታኩቱት ቻሉ። ይህ እንዲሆን ያደረጉት ደግሞ እላይ ያሉት ሰዎች ናቸው። በእኔ እይታ አንድነት የፈረሰው በምርጫ ቦርድ ነው የሚለውን አልቀበለውም። ምርጫ ቦርድ ሊያፈርስ አይችልምና። የእሱ ስራ ማንኛውንም ፖለቲካ ፓርቲዎች በሚተዳደሩበት ህግና ደንብ የሚመራ አካል እንጂ ውስጣዊ ድርጅቱን ሊያፈርስ አይችልም። አንድነትን ምርጫ ቦርድ አፈረሰ የሚሉት ስንኩል አስተሳሰብ ነው። ሃቀኛ የሆነ ቢኖር ኖሮ ድርጅቱን መልሶ ተቀብሎ እንደገና ሊያጠናክር ይችል ነበር።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ 60 በለው 80 ወይም መቶ ፖለቲካ ፓርቲ በጎሳ ቅርጫት የታጎሩትን ጨምሮ የትም የሚደርሱ አይደሉም። አሁን የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄ ሌላ ነው። ጥያቄው ከፖለቲካ ድርጅቶች በላይ ሄዶ ጥያቄውን እና ትግሉን ህዝቡ በባለቤትነት ይዞታል እንጂ ለህዝቡ አለሁልህ የሚልም ሆነ ህዝቡ የእኔ ነው የሚለው ጠንካራ ፓርቲ የለም። አንዳንዶች አለን ለማለት የሚፍጨረጨሩ ሲኖሩ፤ ብዙዎቹ ደግሞ ሽባ ሆነው ከመሸመድመዳቸው የተነሳ ኢህአዴግ ጉያ ውስጥ ተወሽቀው ለራሳቸው የሆነ ስያሜ ሰጥተው ‹‹አለን›› ሲሉ ይታያሉ። እነሱም ሆነ የሚፍጨረጨሩት ሩጫቸው የትም አያደርሳቸውም። በእኔ እይታ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ሊያዋጣ የሚችለው እነዚያ የተበጣጠሱ ሀይሎች መበጣጠሳቸውን ወደ ጎን ጥለው ወደ አንድነት መምጣት ሲችሉ ብቻ ነው። ከዚህ

ውጭ ሊያዋጣ የሚችለው መድብለ ፓርቲ ስርዓት ይህ ብቻ ነው። በአንድ ቤት ውስጥ ሁለት አውራ ብቻ መኖር አለበት ብዬ አምናለሁ፡ ኢትዮጵያ ትልቅ ቤታችን ስትሆን ህዝቡ ካለበት ችግር እና ካለው ጥያቄ እፎይ ሊል የሚችለው ሊመሰረቱ ይገባቸዋል ብዬ ከማስባቸው ሁለቱ ጠንካራ ፓርቲዎች ላይ ሲንጠለጠል ብቻ ነው።

ሰንደቅ፡- ከገዥው ፓርቲ ጋር በፖሊሲና በፕሮግራም የሚለያዩ ሁለት ወይም ሶስት ጠንካራ ፓርቲዎች ቢኖሩ የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ ያድጋል የሚሉ ወገኖች አሉ። በምዕራቡ ዓለም የምናየውም ተመሳሳይ ነው። በጎረቤት ኬንያም የጆሞ ኬኒያታ ቤተሰብና የኦጊንጋ ኦዲንጋ ቤተሰብ የሚመሯቸው ሁለት ፓርቲዎች ብቻ ናቸው ጠንካራ ፍልሚያ የሚያካሂዱት። ይህ ባህል ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጣ ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ፍላጎት የለውም ሲሉ ምክንያታቸውን ያቀርባሉ። ለአብነትም ቁጥራቸው በርከት ያሉ ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲፈርሱ መደረጉን ይገልጻሉ። በእርሰዎ እይታ እውን ፈረሱ የሚባሉት ጠንካራ ፓርቲዎች በሙሉ ከውድቀታቸው ጀርባ ኢህአዴግ አለበት?

ዶክተር ንጋት፡- አሁን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስርዓቱን ስታየው እጅግ አክራሪ ግራ ዘመም ፖለቲካ ነው። ደርግን ድል አድርጎ የመጣው እኮ ህወሓት ነው። ሌሎቹ የኢህአዴግ አባል ፓርቲዎች እኮ የህወሓት ተጨማሪ ክፍሎች (ዲፓርትመንትስ) ናቸው። አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባለው የኢህአዴግ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም የተቀዳው እኮ ከዚሁ ግራ ዘመም ባህሪው ነው። ግራ ዘመም ፖለቲካ ደግሞ በምንም መልኩ ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲ እንዲኖር አይፈልግም። ሊያስተናግድም አይችልም። ነገር ግን ምዕራቡን ለመሰልና ግራ ዘመም ላለመባል ‹መድብለ ፓርቲ› የምትለዋ ሃሳብ ህገ መንግስቱ ላይ ሾልካ ገብታለች። ስለዚህ ከገዥው ፓርቲ ባህሪ የተነሳ ሁሉም ፓርቲዎች ሲፈርሱ እናያለን። ለምሳሌ ብዙ መስዋዕትነት የተከፈለበትና አንጋፋው የፖለቲካ ፓርቲ መኢአድ ሶስት እና አራት ጊዜ ነው የተንኮታኮተው፣ ሰማያዊ አለሁ አለሁ ብሎ ቢታገልም ከሁለት ተከፈለ። አሁን አገሪቱ ላይ ያሉት ሁሉም ህብረ ብሔራዊ ነኝ የሚል ፓርቲ ሁሉ የወጣው ከመኢአድ ነው። ይህ የሆነው ለምንድን ነው? ቢባል በፓርቲዎቹ አመራሮች በሚፈጠር ልዩነት አንዱ ተነስቶ የራሱን ድርጅት ይመሰርታል። ከእሱ ጋር የነበረው ደግሞ ነገ ተነስቶ ሌላ ይመሰርታል። በዚህ ሁሉ ውስጥ የስርዓቱ ሚና እንዳለበት ግልጽ ነው። ምክንያቱም ስርዓቱ ለመድብለ ፓርቲ የቆመ ስርዓት አለመሆኑ እና የዴሞክራሲ ምህዳሩ የጠበበ በመሆኑ ነው።

ፕሮግራምህን ወደ ህዝብ ገብተህ እንድታስተዋውቅ እኮ አይፈቀድልህም። ሁሉንም እንተወው፤ እኔ ባለኝ መረጃ አዲስ አበባ ውስጥ ብቻ 117 ቀበሌዎች አሉ። በእነዚህ የቀበሌ አዳራሾች ለተቃዋሚ ድርጅቶች የተሰጠበትን ጊዜ ሰምተህ ታውቃለህ? በእርግጠኝነት ሰምተህ አታውቅም፤ ምክንያቱም ተሰጥቶ አያውቅማ። በራሳችን ገንዘብ የተከራየነውን ቤት እኮ እንዳንሰራበት አከራዮችን አስፈራርተው እንድንወጣ ተደርጓል። ሌላው ደግሞ አንድ ምሳሌ ልስጥህ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የምታደርገው እኮ ህዝብ ወደ ሰልፉ መጥቶ ፕሮግራምህን እንዲያይና እንዲሰማ በሚያመች ቦታ ነው። እኛ እኮ ጃሜዳ ተሰብሰቡ ተብለናል። እግዚአብሔር ያሳይህ ጃንሜዳ ደግሞ የፌዴራል ፖሊስ፣ አንደኛ ፖሊስ ጣቢያ፣ የክብር ዘበኛ ሆስፒታል፣ የጦር አምባ እና ምኒልክ ሆስፒታል ያለበት ነው። እዚያ ሜዳ ውስጥ ማን ሊመለከት ነው ሰላማዊ ሰልፍ የምታደርገው? ስለዚህ ይህ አምባገነን ስርዓት ስለሆነ ለህዝብ የፕሮግራም እና የፖሊሲ አማራጭ የሚያቀርቡ ጠንካራ ፓርቲዎች እንዲኖሩ ሊፈቅድ አይችልም። ምክንያቱም ይህ ሥርዓት መሰረቱ አክራሪ የግራ ዘመም ፖለቲካ ነው።

ቀደም ሲል ያነሳኸው የኬንያ ሁለቱ ፓርቲዎች መሪዎቹ በመካከላቸው የተፈጠረውን ውዝግብ እና የፓርቲዎቹን ታሪካዊ እንቅስቃሴ ማንሳቱን ትተን ከምርጫው ማግስት በኋላ በአፍሪካ ታሪክ መጀመሪያ የሆነውን ውሳኔ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ በኋላ ምርጫው ተደገመ። ከድጋሚ ምርጫው በኋላ በተፈጠረው ግጭት ብዙ ሰው ቢጎዳም ሁለቱ የፓርቲዎቹ መሪዎች ኡሁሩ ኬኒያታ እና ራኢላ ኦዲንጋ ቆም ብለው አሰቡና የሁለታችን ልዩነትና ውዝግብ ለአገራችንና ለአገራችን ህዝብ አይበጅም፤ ስለዚህ እንወያይ ብለው ተወያዩ። ለአገራቸውም መፍትሔ ለማምጣት ወደ ሰላም መጡ። ይህ የኬንያዎች አካሄድ ትምህርት የሚሆናቸው ከሆነ የእኛ ገዥዎችም ቆም ብለው ለህዝብ አማራጭ ማምጣት የሚችል የፖለቲካ ምህዳር ሊፈጠርለት ይገባል። ከዚህ ውጭ ግን ደርግ እንዳደረገው ማርክስን በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ መጫን ውጤት የሌለው ላብራቶሪ ነው የሚሆነው። አንድ እኔን ብቻ እወቅ፣ እኔን ተከተል እና እኔን ስማ የሚል ቆሞ ቀር አስተሳሰብ የተጠናወተው ፖለቲካ በአገራችን ለተፈጠረው ችግርም ምክንያት ሆኗል።

ሰንደቅ፡- ህዝቡ ትግሉን በባለቤትነት ይዞታል ብለዋል። ቀደም ባሉት ቀናትም የቀድሞው የአንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ አመራር የነበሩት አቶ አንዷለም አራጌ ‹‹ኢህአዴግ ትግሉን ከፓርቲዎቹ ወደ ህዝቡ አውርዶታል›› ሲሉ ተናግረዋል። ይህን ሃሳብ በተደጋጋሚ ጊዜ ምሁራን ሲናገሩ ይሰማል። ትግሉ ከፓርቲዎቹ ወደ ህዝቡ የወረደው በፓርቲዎች መዳከም ነው ብለን ልንወስደው እንችላለን?

ዶክተር ንጋት፡- እኔ በመሰረቱ የማምነው ትግሉ ወደ ህዝቡ እንዲወርድ የተደረገው የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በመድከማቸው ሳይሆን ስርዓቱ ፖለቲካ ድርጅቶቹን ስለገደላቸው ነው። ለዚህ ነው ለዚህ ሁሉ ችግር እና ሁከት መነሻው ስርዓቱ ነው የምለው። ቀደም ብዬ እንደነገርኩህ የፖለቲካ ምህዳሩን ቆልፎ ፓርቲዎቹ እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓቸዋል። በዚህ ምክንያት ፓርቲዎቹ ራሳቸውን አጠናክረው ከህዝብ ጋር በመገናኘት ትግሉን እንዳይመሩ ያደረገው ገዥው ፓርቲ ነው።

ሰንደቅ፡- እርስዎ ከሚሉት በተቃራኒ የዴሞክራሲ ምህዳሩ መስፋቱን ለማረጋገጥ በአገራችን በተከፈተው የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በርካታ ፓርቲዎች ተደራጅተው እየተንቀሳቀሱ ነው ሲል ኢህአዴግ ይናገራል። ከዚህ በተጻዳኝ ደግሞ ኢህአዴግ ራሱን አውራ ፓርቲ ብሎ ሰይሞ ሌሎች እንዳይንቀሳቀሱ በጥላው ከልሏቸዋል ሲሉ የሚሞግቱ አሉ። በዚህ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ይስጡን እስቲ?

ዶክተር ንጋት፡- በመሰረቱ አውራ ፓርቲ የአንድ የዴሞክራሲ ባህል መገለጫውም አይደለም። አውራ ሆኖ የወጣው ብዙዎቹን ጨፍልቆ ነው። ስርዓቱ እኮ ገዥ መደብ ነው። የአገሪቱን ሀብት በሙሉ የያዘ ፓርቲ ነው። ሚዲያው የእሱ ነው፤ ብሩ የእሱ ነው፤ ንብረቱ በሙሉ የእሱ ነው። ነገርኩህ እኮ አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ አንድ የቀበሌ አዳራሽ ይጠቀማል እንዴ? የትኛው ተቃዋሚ ፓርቲ ነው ተሰብስቦ ፕሮግራሙን ለህዝብ እንዲያስተዋውቅ ያደረገው? ይህ ብቻ እኮ አይደለም። የታሰሩት ፖለቲከኞች በዚህ ምክንያት እኮ ነው የታሰሩት። ስርዓቱ ለዚህ የቆመ ስላልሆነ አይፈቅድም። ለዚህ እኮ ነው ችግሮቹ እየተጠራቀሙ ሄደው እዚህ የደረስነውና አገሪቱን መስቀለኛ መንገድ ላይ እንድትወድቅ ያደረጋት።

ሰንደቅ፡- በዚህ የተነሳ አገሪቱ መስቀለኛ መንገድ ላይ ከሆነችና የችግሩ ስፋትም እየበዛ ነው ካልን መፍትሔው ምንድን ነው?

ዶክተር ንጋት፡- አሁን የተነሳውን ችግርና እየነደደ ያለውን ጥቁር እሳት ሊበርድ የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ ገዥው ፓርቲን ጨምሮ ሁሉንም የአገሪቱ ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት የሀይማኖት ተቋማት መሪዎች፣ የራሳቸው ፕሮግራም ያላቸው ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ አባ ገዳዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች፣ ትልልቅ ምሁራን እና የፖለቲካ ሰዎች ቁጭ ብሎ መወያየትና መፍትሄ ማምጣት ሲችሉ ነው። ኢህአዴግ እኮ ችግር ሲመጣ ችግሩ የእኔ ነው ይልና መፍትሔውም እኔ ነኝ ዝም ብለህ ስማ የሚል ፓርቲ ነው። እኛ ደግሞ ጉዳዩ ስለሚመለከተን ዝም አንልም ነው የምንለው። ትጥቅ ያነሱት የፖለቲካ ድርጅቶችም ቢሆኑ ህዝቡ አልፈልጋችሁም ይበላቸው እንጂ በአገራቸው ጉዳይ ስለሚመለከታቸው እነሱንም ያካተተ በጠረጴዛ ዙሪያ የሚደረግ ውይይት ሊከፈት ይገባል ብዬ አምናለሁ። የህዝብ ሉአላዊነት ሊከበር የሚችለው በወከላቸው ተወካዮቹ አማካኝነት ብቻ ነው። በማንኛውም አገር የህገ መንግስቱ የበላይ አካል ህዝብ ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ በአንድ ዓመት ተኩል ውስጥ ሁለት ጊዜ ነው አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታወጀው። ከዚህ በፊት ‹‹አይደገምም›› የሚል ጽሁፍ በካናቴራ ተጽፎ ልጆቻችን ያንን ለብሰው ከእስር ወጡ። አሁን ያ ድራሹ ጠፍቷል። ከዚያ በኋላም ጥልቅ ተሃድሶ በለው፣ የካቢኔ ለውጥ በለው፣ ለወርና ከዚያ በላይ የፈጀ ግምገማም ተካሄደ ውጤት አልመጣም። ሰሞኑን ደግሞ በሞያሌ ከተማ በተሳሳተ መረጃ ዘጠኝ ሰዎች ተገድለዋል ተባለ። አንድ ወታደራዊ ኦፕሬሽን በተሳሳተ መረጃ ይህን ያህል ሰው እንዴት ሊገድል ይችላል? አንዱ ራሱ እኮ ያስጠይቃል፤ እንኳን ያን ያህል ህዝብ አልቆ። የወንጀሉ ፈጻሚዎች ተይዘው ምርመራ እየተካሄደባቸው ነው መባሉ አይደለም ቁም ነገሩ። ትልቁ ቁም ነገር የእኔ መብት እስከምን ድረስ ነው የሚከበርልኝ? የሚለው ነው። ይህን ተከትሎ ወደ ኬንያ ስደት ቀጥሏል። ችግሩ በሌላ አካባቢ ቢፈጠርም ወደ ሌላ አጎራባች አገር ስደት መስፋፋቱ አይቀርም።

ስለዚህ አሁን ያለው ችግር የኢህአዴግ አጀንዳ መሆን የለበትም። አጀንዳው የህዝቡ መሆን አለበት። ምክንያቱም ህዝብ መፍትሔ ይፈልጋል፤ ከበርካታ ምሁራን ጋር ስንገናኝ የምናደርገው ውይይት ይህ ነው። መንግስትም ይህን ተረድቶ ከህዝብ ጋር ይሁን፤ የውይይት መድረክ ይከፈት። በአገራችን እኮ አኩሪ የሽምግልና እና የውይይት ባህል አለን። የአባ ገዳ እና የአገር ሽማግሌዎች የቆየ አኩሪ ባህል ይህን ችግር ሊያቆም ይችላል እንጂ በጠብመንጃ ችግሩን እና ተቃውሞውን ልታቆመው አትችልም። ሰላምን በጥይት አታስከብረውም። ስለዚህ እኔ የምለው ‹ደም ማፍሰስ ደም ያፈላል› እና የአገራችን ጸጥታ ሀይል በማያስፈልግ ተልእኮ ውስጥ አይግባብን። እሱም ቢሆን ሰላም ይፈልጋል።

ሰንደቅ፡- ለችግሩ ብቸኛው መፍትሔ ሁሉን አቀፍ ውይይት ነው ቢሉም፤ በኢህአዴግ በኩል ያለው አቋም ግን ከዚህ የተለየ ነው። ከእስካሁኑ የኢህአዴግ ባህሪ ተነስተን በእርስዎ ሃሳብ ተስማምቶ ኢህአዴግ ሁሉን አቀፍ ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋል ብለው ያስባሉ?

ዶክተር ንጋት፡- ላለፉት ረጅም ዓመታት በኢትዮጵያዊነት ብሔርተኝነት ላይ ሳይሆን በልዩነት ላይ ሲሰበክ ቆይቷል። ያ ልዩነት ደግሞ እያበጠ ሄዶ ወዳላስፈላጊ ብሔርተኝነት ሄዷል። ይህ ደግሞ ወደማንወጣው መንገድ እየወሰደን ነው፤ ምልክቶችም እየታዩ ነው። ይህንን ችግር ለመፍታት በረጅም ዘመን አኩሪ የውይይት ባህል እና በሰለጠነ የፖለቲካ እይታችን ማርገብ የሚችለው ቀደም ሲል የጠቀስኩልህ ሀይሎች ብቻ ናቸው። ወደ ኢህአዴግ ባህሪ ስንመጣ ለሰላምና ለዴሞክራሲ መፍትሔ እኔ ብቻ ነኝ፤ ችግሮቹ ከአቅሜ በላይ ቢሆኑ ደግሞ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እመክተዋለሁ፤ የሚል አቋም ነው ያለው። ያ ደግሞ አያስኬድም፤ የመጠፋፋት ነገር ይመጣል። አገራችን ያለችበት

ጂኦፖለቲካል አቀማመጣችን እጅግ አደገኛ ሁኔታ ውስጥ ነው ያው።

በአካባቢያችን በጅቡቲ፣ በኤርትራ፣ በሶማሊያ እና በደቡብ ሱዳን ሳይቀር የጦር ሰፈር እየተገነባ ነው። ይህ ደግሞ በተዘዋዋሪም ቢሆን ይመለከተናል። እስካሁን ሆኖ በማያውቅ ሁኔታ ቱርክ እና ግብጽ ሳይቀሩ በኤርትራ እና በደቡብ ሱዳን እንዲሁም በሶማሊያ የወታደራዊ መንደር ወደ መገንባት ሄደዋል። ከዚህ በተጓዳኝ ደግሞ በአካባቢያችን አሸባሪ ቡድኖች እንደ አልሻባብ፣ አልቃኢዳ፣ ቦኮሃራም እና አይሲስን የመሳሰሉት እስላማዊ አክራሪ ቡድኖች ለእኛ ስጋቶች ናቸው። የእነዚህን ሁኔታዎች አሳሳቢነት የተረዱት ሩሲያ እና አሜሪካ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቻቸው በኩል ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከመንግስት ጋር የተነጋገሩትም ለዚህ ነው። አካባቢው አስፈሪና አሳሳቢ በመሆኑ የኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ በሰላም መፈታት እንዳለበት ያምናሉ። ቀደም ባሉት ዘመናት በአጼ ኃይለሥላሴ ጊዜ የገለልተኝነት ሚና እንጫወት ነበር። አሁን ግን ወደንም ሆነ ሳንወድ የግድ ከሁሉም እያጣቀስን ነው የምንኖረው። ይህ ማጣቀሱ ደግሞ ይህን ህዝብ ይጎዳል። ስለዚህ ይህ ስርዓት ረጋ ብሎ ማሰብ አለበት።

በሌላ በኩል በአገራችን የአመራሮች አለመስማማት ያለ ይመስለኛል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የግንባሩ ሊቀመንበር በመሆናቸው የፖለቲካ መሪ ናቸው። በተመሳሳይ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ናቸው። እዚህ ላይ ግን ህዝቡ በትክክል በማያውቀው ነገር ‹ለቅቄያለሁ የተሻለ ሰው ይይዝ› ማለታቸው መልካም ነው። ነገር ግን ከመልቀቂያቸው ውሳኔ ጀርባ ያለ አንድ ሀይል እንዳለ ነው የምረዳው። የዚያን ሀይል ማንነት እና ፍላጎት በግምት የምትናገረው ሳይሆን ወደፊት ታሪክ የሚያወጣው ነው የሚሆነው። ስለዚህ በአሁኑ ሰዓት የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እያካሄደ ባለው ስብሰባ የግንባሩን ሊቀመንበር መርጦ ለአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ያቀርብና ለፓርላማ አቅርቦ ያስጸድቃል። በዚህ ጉዳይ ላይ ፓርላው ከማጽደቅ የዘለለ ሚና የለውምና። ነገር ግን ፓርላማው ላይ እንደቀደመው ጊዜ ሁሉንም ከመቀበል ወጣ ያለ አቋም ሲያራምድ ለመጀመሪያ ጊዜ ባለፈው አስቸኳይ ስብሰባ ላይ አየን። ይህ ባህል በግራ ዘመም ፖለቲካ ያልተለመደና ሆኖ የማያውቅ ነው። ይህ የሚያሳየው የሆነ ነገር እንዳለ ነው። ይህም አንዳች የአመራር ፍትጊያ እንዳለ እረዳለሁ። ስለዚህ እነዚህ ሁኔታዎች ውጤታቸው የከፋ ሊሆን ስለሚችል ይህ ስርዓት ለሰላምና ለአገር ሲባል ከኡሁሩ ኬኒያታ መማር አለበት። በደልም ቢኖር ተቻችሎ መኖር እና የህዝቡን ጥያቄ ረጋ ብሎ አዳምጦ መመለስ እንጂ በምንም መልኩ አንድ ጎሳ ነጥሮ እንዲወጣ ሌላው እንዲታፈን የስልጣን ጥያቄ መሆን የለበትም። ስለዚህ ይህ ስርዓት መያዝ ያለበት አጠቃላይ የ 27 ዓመቱ ቀውስ እዚህ ደረጃ ደርሷል። ይህንም ገምግሞታል።

ተቃዋሚዎች የሚገባቸውን ቦታ አላገኙም፤ ህዝቡም በአገሩ ጉዳይ በትክክል የሚወያይበት መንገድ አልፈጠርንለትም ሌላው ደግሞ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዳለ ተገልጿል። የመልካም አስተዳደር ችግር ሲባል ደግሞ ሙስና፣ ኪራይ ሰብሳቢነት እና የሲቪል ሰርቪሱ መዋቅር ማለት ነው። እኔ እንዲያውም የምሰጋው አሁን ያለው ከፍተኛ የሆነ ሙስና እና ኪራይ ሰብሳቢነት በፌዴራል እና በክልል ደረጃ የሚበላው ከፍተኛ ገንዘብ ወደ ወረዳ ደረጃ ከወረደ አገር ጠፋ ማለት ነው። አሁን እያየን ያለውም ወደ ወረዳ እየወረደ መምጣቱን አመላካች የሆኑ አስፈሪ አዝማሚያ እያየን ነው። ምክንያቱም ወረዳ ላይ የመሬት ጉዳይ አለ ሌሎች ሰፊ የሀብት ምንጮችም ያሉት ወረዳ ላይ ነው። እዛ ላይ በደንብ አልተሰራም። ስለዚህ አገርን ሊያፈርስ የሚችል ክፉ የሙስና መንገድ ስለሆነ ያንን መዋጋት ያስፈልጋል። እነዚህ ሁሉ ችግሮች ያሉበት መንግስት ሊወስደው የሚገባው እርምጃ በሩን ለውይይት ክፍት ማድረግ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ለራሱም ህልውና ይጠቅመዋል እንጂ አይጎዳውም።

ሰንደቅ፡- በቅርቡ በአንድ መድረክ ላይ ተገኝተው ስለ አድዋ ድል ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበው ነበር። በጥናትዎ ሲገልጹም የአጼ ምኒልክን የክተት አዋጅ ተንተርሰው ሲያቀርቡ የጣሊያን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ‹‹አገርን የማጥፋት እና ሀይማኖትን የመለወጥ አላማ›› እንዳለው ገልጸዋል። ለዚህ የሚያቀርቡት ማስረጃ ምንድን ነው?

ዶክተር ንጋት፡- በተለያየ ምክንያት ስትበጣጠስ የነበረች አገር እንደገና አንድ የሆነችው በአጼ ምኒልክ ነው። እሳቸው የአገሪቱ ንጉሰ ነገስት መሆናቸውን ካወጁ በኋላ ለሌሎቹ ክፍላተ ሀገራት የአገሬው ተወላጅ እንዲያስተዳድር ሙሉ ሙብትና ስልጣን ሰጥተዋል። በየግዛቱ ያሉ አስተዳዳሪዎች ግብራቸውን መገበር እንጂ በአስተዳደሩ ውስጥ ንጉሰ ነገስቱ ጣልቃ አይገቡበትም። በዚህ የተነሳም በእሳቸው ዘመን ‹እንዘጭ እምቦጭ› የሚል የግዛት አስተዳዳሪ አልነበረም። ይህ የሆነው በንጉሰ ነገስቱ ብልሃት ሲሆን ለዚህ ደግሞ የእሳቸው አማካሪ የነበሩት የመሳፍንት የዘር ሀረግ ያላቸው ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ብጡል አማካኝነት ነው።

ወደ አድዋ ድል ጥያቄህ ስመጣ በበርሊኑ አፍሪካን የመቀራመት ኮንፈረንስ መሰረት አውሮፓዊያን በ1811 በጀመሩት የኢንዱስትሪ አብዮት ለኢኮኖሚያቸው እድገት ጥሬ ሀብት ፍለጋ ላይ ነበሩ። ይህን ደግሞ በአንድ ቀን ተነስተው ያካሄዱት ፕሮጀክት ሳይሆን የ50 እና የመቶ ዓመት እቅድ የተያዘለት ፕሮጀክት ነው። በሀይማኖት፣ በአሳሽነት፣ በፖለቲካ፣ በወታደራዊ ስልጠና፣ በህክምና እና በተለያዩ መንገዶች የአህጉሩን መውጫ መግቢያ አጥንተዋል። ጣሊያንም ኢትዮጵያን ለመያዝ ስትመጣ ከኮንፈረንሱ እንደወጣች ቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ አልመጣችም። ለመቶ ዓመት የአገሪቱን መውጫ መግቢያ ስላጠናች ነበር። የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 ለጦርነቱ መነሻ ይሁን እንጂ ውሉ ባይኖርም ጦርነቱ መነሳቱ እንደማይቀር በፖሊሲ ደረጃ የተሰራበት ነበር። አጼ ዮሃንስ ወደ ሱዳን መዝመታቸውን ተከትሎ ምጽዋ የነበረው የጣያን ጦር አስመራን ያዘ። ከዚያ ከ1887 ጀምሮ ከአስመራ ወደ አዲግራት፣ ከዚያም ወደ መቀሌ፣ ከመቀሌ አምባለጌን እየያዘ ግዛቱን አስፋፍቷል። በዚህ ጊዜ አገሪቱ ውስጥ ርሃብ መነሳቱ እና እንስሳቱ ስለተጎዳ ንጉሰ ነገስቱ የወሰዱት እርምጃ አልነበረም። ነገር ግን ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ያስተላለፉት መልዕክት ነበር እሱም የውጫሌን ውል አንቀጽ 17 እንደማይቀበሉትና ጣሊያንም የመስፋፋት ስራውን እንዲያቆም የሚገልጽ ነበር።

የንጉሰ ነገስቱን ጥሪ ስንመለከት ‹‹… በእግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጥም። አገር የሚያጠፋ፣ ሀይማኖት የሚለውጥ ጠላት መጥቶብሃል፤ ለአገርህ፣ ለሚስትህ እና ለልጅህ ስትል ጉልበት ያለህ በጉልበት ጉልበት የሌለህ በጸሎት እርዳኝ ወስልተህ የቀረህ ግን አልተውህምለዚህ አማላጅ የለኝም ማሪያምን አልምርህም›› ሲሉ የክተት አዋጅ አወጁ። እዚህ ላይ አገር የሚያጠፋ የሚል ሀረግ አለ። ጣሊያን በያዘው የቅኝ ግዛት አስተዳደር በሰራው ካርታ ኤርትራን ከትግራይ ጋር አቀናጅቶ አንድ ግዛት፤ ወሎ፣ ጎንደርና ጎጃምን በአንድ፤ ሸዋን ለብቻ፤ ጅማን ይዘህ ሲዳሞን መላውን እስከ ወለጋ እና ጉሙዝ በአንድ፤ አርሲ ባሌን ይዘህ እስከ ሀረርጌ ለብቻ፤ የኢትዮጵያን 1/5 ኛ የሚሆነውን የኦጋዴንን ግዛት ከሞቃዲሾ ጋር ቀላቅሎ አንድ ግዛት አድርጎ ኢትዮጵያን ከአምስት ከፍሎ ነበር ሊገዛ የነበረው። እዚህ ላይ ኢትዮጵያ እንድትጠፋ አልተደረገም? ዓላማው በትክክል ኢትዮጵያን ለማጥፋት እንደሆነ ግልጽ ነው።

አድዋ ላይ ድል ከሆነ በኋላ በድጋሚ ከ40 ዓመት በኋላ በፋሽሽት አማካኝነት በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ሲጀምር

በአንድ ቀን ብቻ ከሶስት ሺህ በላይ የደብረ ሊባኖስ መነኮሳትን የገደለው ጣሊያን ነው። አቡነ ጴጥሮስን የገደላቸውስ ጣሊያን አይደለም? የኤሊባቡሩን አገረ ስብከት አቡነ ሚካኤልን የገደላቸውም ጣሊያን አይደል እንዴ? ታዲያ እዚህ ላይስ ሀይማኖትን ለማጥፋት አልተነሳም? ለዚህ ነው ንጉሰ ነገስት አጼ ምኒልክ አገር የሚያጠፋ ሀይማኖት የሚለውጥ ጠላት ሲሉ የገለጹት። በአገሩ እና በሀይማኖቱ ድርድር የማያውቀው የአገራችን ህዝብም ለዚህ ነው ከወላይታ አድዋ፣ ከሐረር አድዋ፣ ከሲዳሞ ከከምባታ፣ ከወለጋ፣ ከባሌ ከጎጃም አጠቃላይ ከመላው አገራችን ተነስቶ አድዋ ድረስ በራሱ ስንቅ፣ ትራንስፖርት እና ትጥቅ የዘመተው።

ኢትዮጵያ አሁን ባለችበት መልኩ እና በቆየ ማንነቷ ተጠብቃ እንድትቆይ የተደረገው በዚያ መልኩ በተካሄደ ትግል በተገኘው የአድዋ ድል ኩራታችን ነው። ይህ ደግሞ የንጉሰ ነገስቱ ጥሪ ትክክለኛ እና የህዝባችን አገር ወዳድነት ያስገኘው ውጤት ነው።